# “የሀገር ልማት በሀገሩ ልጆች!!”

ከላሊ ደስአለኝ 08-24-14

ቻይና 35 ሚሊዬን የሚሆኑ ዜጎቿ በተለያዩ የዓለማችን ሀገራት ይኖራሉ። በዚህም ቻይና ከአለም ሀገራት ከፍተኛውን 00ቁጥር ያላት ሀገር ሆናለች። እነዚህ ስደተኛ ዜጎቿ በሀገሪቱ ልማትና ብልጽግና የጎላ አስተዋጽኦ የነበራቸው ባይሆንም የኋላ ኋላ የቻይና ሪፐብሊክ መንግስት ባቀረበው የልማት ጥሪ መሰረት በሀገራቸው ቀጥታ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች በመጠቀም አሁን ያለው ታላቁን የቻይና ኢኮኖሚ በመገንባት ረገድ አይነተኛ ሚና ። በወቅቱ በተለያዩ ክፍላተ-አህጉር ይሆሩ የነበሩ ቻይናዊያን ምሁራን፣ ባለሙያዎችና ባለሀብቶች ያላቸውን ዕውቀት ፣ ልምድ፣ ክህሎትና መዋዕለ ነዋይ በሀገራቸው በማፍሰስ ግዙፍ አለም አቀፍ ኩባንያዎችን ለማቋቋም በቁ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ2002 48 ቢልዮን የሚሆነው በቻይና ምድር ኢንቨስት የተደረገው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ካፒታል በቻይናውያን ዲያስፖራ አማካይነት የመጣ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቻይናውያን ዲያስፖራዎች ያቋቋሟቸው፤ ኩባንያዎች በአለም አቀፍ ገበያዎች ሳይቀር፤ የላቀ የተወዳዳሪነት አቅም እንዲኖራቸው ተደርገው የተገነቡ ነበሩ። በአሁኑ ወቅትም በየትኛውም የአለማችን ክፍል ስንሄድ የምናገኛቸው ቻይናዊያን ባሉበት ቦታ ሆነው ለሀገራቸው ልማትና ብልፅግና አበክረው ይሰራሉ። በተለይም በታዳጊ ሀገራት በሚከናወኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ስራ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ በርካታ የቻይና ኩባንያዎች ምንጫቸው የቻይናውያኑ ዲያስፖራ ዕውቀትና ካፒታል መሆኑ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ለቻይና ኢኮኖሚ ግንባታ የጀርባ አጥንት ሆኖ ይኖራል።

በአለም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛ ዜጋ ካላቸው ሀገራት አንዷ የሆነችው ህንድም ዜጎቿ ባሉበት ሆነው ለአንድ አላማ ይሰራሉ። ያ አላማ ደግሞ ለህንድ ኢኮኖሚ እሴት መጨመር ነው። በተለያዩ ክላተ-አህጉር የሚገኙ የህንድ ዲያስፖራዎች ለረºም ጊዜ ባዳበሩት የቁጠባ ባህል ተጠቅመው የቆጠቡትን ገንዘብ በየጊዜው ወደ ሀገራቸው ባንኮች ገቢ ማድረግ አልያም በህንድ ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው መላክ ተቀዳሚ ስራቸው ነው። በዚህም ከሀገሪቱ ዓመታዊ የምጣኔ ሀብት ጭማሪ የአንበሳውን ድርሻ

የሚወስደው ይህው በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ህንዳውያንና ትውልደ- ህንዳውያን የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ ነው። ከ 15 ዓመታት በፊት 20 ሚሊዮን የሚሆኑ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ህንዳዊያን 35 በመቶ የሀገሪቷ የዓመት ገቢ የሚሸፍን ገቢ የነበራቸው ናቸው። ሆኖም ግን እ.አ..አ በ2000 የህንድ መንግስት ባደረገው ጥናት መሰረት ዜጎቹ ከቻይናና ሜክሲኮ ዜጎች ያነሰ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ አቅም እንዳላቸው ተረጋገጠ። በዚህም የህንድ መንግስት ባደረገው የፖሊሲ ማሻሻያ መሰረት ዲያስፖራዎች ወደ ሀገር ውስጥ በመሳብ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ተጋበዙ። ህንድ በአሁኑ ሰዓት ፈጣን የኢኮኖሚ እመርታ እያስመዘገቡ ከሚገኙ እንዲሁም ከፍተኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ አገር አንዷ ለመሆን በቅታለች።

የህንድ ዜጎች ወደ ሀገራቸው ከሚልኩት የውጭ ምንዛሬ ባሻገር ባደጉት ሀገራት በነበራቸው ቆይታ ያካበቱትን ልምድና ዕውቀት ወደ ሀገራቸው እንዲገባ አድርገዋል። ህንድን በአምላክ ዓይን እንዳየ የሚያምኑበት ታላቁ መሪያቸው ጋንዲ ሁሌም በስነ-ልቦናቸው ዘመን አይሽሬ ተፅእኖ አሳድሮባቸዋል። ማንኛውም ህንዳዊ ባለበትና በሄደበት ቦታ የሀገሩ ምርት ይገዛል፣ የሀገሩን ወግና ባህል ያከብራል። ለዚህም ነው ህንዳዊ ዲያስፖራዎች ከተለያዩ የዓለማችን ክፍል ያገኙት ልምድና ዕውቀት በመቀመር ለሀገራቸው ዕድገትና ብልጽግና ደፋ ቀና የሚሉት።

ከቻይናና ህንድ ቀጥሎ ከፍተኛ የስደተኛ ዜጎች ሀገር የሆነችው የላቲን አሜሪካዊቷ ሜክሲኮ ነች። ሜክሲኮ ዜጎቿ በብዛት የሚሰደዱባት ሀገር አሜሪካ ብትሆንም ወደ ሌሎች የዓለማችን ሀገራትም ይሰደዳሉ ። የስደታቸው ዋና ምክንያትም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነበር። በሀገሪቱ የነበረው አፋኝ ስርዓት የፈጠረው ኢ-ፍትሀዊ አሰራር ዜጎችን በማስመረር ለስደት የዳረገ ክስተት ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ ለዘመናት ትተዳደርበት የነበረው የግብርና ዘርፍ ኋላቀር ሆኖ በመቆየቱ የድህነት፣ የረሀብና የጉስቁልና ሲሳይ ሆነው የቆዩ ዜጎች አማራጫቸው የዕለት ጉርስ ወደሚያገኙበት ሀገር ድንበር አቋርጦ መሻገር ነበር። ይህንኑ ክስተት የተገነዘበው አዲሱ የሜክሲኮ መንግስት ከ እ.አ.አ 1998 ጀምሮ በተለያዩ ክፍላተ-ዓለም የሚገኙ ዜጎቹና ትውልደ-ሜክሲኮ ማደራጀት ጀመረ። በዚህም ዜጎቹ ስለ ሀገራቸው የነበራቸው የተዛባ ግንዛቤ ሚዛናዊ እንዲሆን ለማድረግ ቻለ። በመቀጠል የሜክሲኮ መንግስት በተለያየ ሀገራት በከፈታቸው ኢምባሲዎች፣ ቆስላ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ዲፕሎማሲያዊ

ልዑኮች ምክንያት ልዩ ልዩ የልማት ትብብር ፕሮግራሞች ቀረጸ። ዜጎቹም በያሉበት ሆነው የሀገራቸው መልካም ገፅታ የሚገነቡ አምባሰደሮች ሆኑ። የሜክሲኮ የተፈጥሮ ችሮታ፣ የአማዞን ወንዝና ጥቅጥቅ ጫካው ቱርፋቶች እንደዚሁም የሀገሪቱ የቀድሞ ስልጣኔ ገናናነት የሚያወሱ መረጃዎች በዓለም መገናኛ ብዙኃን ከዳር እስከዳር ናኙ። በዚሁ መንገድ ሜክሲኮ ከዓመታት በኋላ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እመርታ የምታስመዘግብ ታላቅ ሀገር መሆኗ እውን ሆነ።

ከሰባቱ ቀደምት የዓለም ስልጣኔ መናፀሪያ አንዷና የሰው ዘር መገኛ የሆነችው ኢትዮÉያም በታሪክ ባለ ገናና መንግስትና ታላቅ ተፅእኖ ፈጣሪ ሀገር የነበረች መሆኗን የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ። የኋላ ኋላ በተፈጠረ የገº መደቦች ንቅዘት ኢትዮÉያ የዓለም የስልጣኔ ቁንጮ የዓለም ጭራ ሆና ዜጎቿ ለረሀብ፣ ለችነፈርና ለዕልቂት የተዳረጉበት የታሪክ ክስተት መቸውም ቢሆን ከኢትዮÉያውያን ልቦና የማይጠፋ ጉዳይ ነው። በዚህም ሀገራችን ዜጎቿ የሚኮሩበት በመሆን ፈንታ የሚያፍሩባትና የሚሸማቀቁበት የድርቅና የረሀብ ምሳሌ እስከ መሆን ደርሳ ነበር። አእላፍ ኢትዮÉያውያን የዕለት ጉርሳቸውንና የቀን ልብሳቸው ወደሚያገኙባቸው ሀገራት ለአስከፊው የስደት ኑሮ ተዳርገዋል።

በኢትዮÉያ ስደት ሲጀመር በርካታ ዘመናት እንዳስቆጠረ የሚገመት ቢሆንም በንጉሱ ዘመነ-መንግስትና በወታደራዊው የደርግ መንግስት የአገዛዝ ዘመን በእጅጉ የገነነበት ወቅት ነበር። በንጉሱ ዘመነ-መንግስት ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲገነባ በሚቀርቡት ጥያቄዎች ሳቢያ የፈሰሰው ንጹህ ደም የተመለከቱ ሞሁር ኢትዮÉያውያን በወቅቱ ሳይውሉ ሳያድሩ የስደት ኑሮ እንዲመርጡ ምክንያት ሆኖ ነበር። ሆኖም ግን ፊውዳሉ ስርዓት በጭቁኑ ህዝቦች የተባበረ ክንድ በተቀጣጠለው ህዝባዊ አብዮት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግብአተ- መሬቱ ሲበሰር ኢትዮÉያውያን ዲያስፖራ የማይናቅ ሚና እንደነበራቸው አይዘነጋም። በህዝባዊ አብዮቱ ማግስት መርህ ባልተከተለ አኳኃን ወደ ስልጣን ብቅ ያለው የደርግ መንግስት ከጊዜአዊ አስተዳዳሪነት አልፎ ወደ ፍጹም የለየለት አምባገነናዊ ስርዓት ሲሸጋገር በነበሩ አመታትም በርካታ ኢትዮÉያውያን ሀገር ለቀዋል።

ደርግ መንበረ-ስልጣኑን በጨበጠ ማግስት በሀገሪቱ ፖለቲካል ኢኮኖሚ አማራጭ ሃሳብ ይዘው የሚመጡ ማናቸውም ኃይሎች እውቅና መስጠት ቀርቶ ገና በእንጭጩ ለመቅጨት መጠነ-ሰፊ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረ። ህዝባቸውንና ወገናቸውን ለማገልገል የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና አመራር ሆነው ሲሰሩ የቆዩ በርካታ ምሁር ኢትዮÉያውያን በለጋ እድሜያቸው ተቀጭተዋል። ከእስርና ግድያ ያመለጡት ዜጎች ደግሞ ጊዜ ሳይሰጡ እግራቸው ወደ መራቸው ሀገር የተሰደዱ በርካቶች ናቸው። ቀይ ሽብር ሰለባነት ራሳቸውን ለማዳን የስደት ኑሮ የመረጡት እነዚህ ዜጎች ስለ ሀገራቸው ሁኔታ የነበራቸው አመለካከት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተዛባ ሆኖ ቆይቷል።

በአሁኑ ሰዓት ሀገራችን ወደ ቀድሞ ገናናነቷ በምትመለስበት የህዳሴ ጎዳና ላይ በፍጥነት በመጓዝ ላይ ነች። በተለያዩ ክፍላተ-አህጉር የሚገኙ ኢትዮÉያውያንና ትውልደ-ኢትዮÉያውያንም በዚሁ ረገድ ሰፊ ግንዛቤ ፈጥረዋል። በመሆኑም ከትጥቅ ትግል ጀምሮ ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመገንባቱ ሂደት የኢትዮÉያውያን ዲያስፖራዎች ሚና ከፍተኛ ነበር። የኢፌዲሪ መንግስትም በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮÉያንና ትውልደ ኢትዮÉያን በሀገራቸው ልማትና ብልጽግና ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው የሚያስችል የዲያስፖራ ፖሊሲ በማውጣት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ፖሊሲው በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮÉያውያንና ትውልደ-ኢትዮÉያውያን በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም፣ በሀገር ገጽታ ግንባታ ፣ በዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲሁም በሌሎች የሙያ መስኮች ህዝባቸውንና ወገናቸውን እንዲያገለግሉ የሚያበረታታ ነው። በዚህም ከተሃድሶ በኋላ ባሉት ዓመታት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ዲያሰፖራዎች በሀገራቸው የቀጥታ ኢንቨስትመንት ተዋናይ በመሆን አመርቂ ድሎች እያስመዘገቡ ይገኛሉ።

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ የክልሉ ተወላጅ ኢትዮÉያንና ትውልደ ኢትዮÉያውያን የልማት ጥሪ በማቅረብ ከሀምሌ 24-30/2006 ዓ/ም በመቐለ ከተማ ታላቅ የልማት ድግስ አዘጋጅቶ ነበር። ፌስቲቫሉ የትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን አሜሪካ በየዓመቱ ሰሜን አሜሪካ በሚገኙ ከተሞች ሲካሄድ የቆየ ቢሆንም፤ ዘንድሮ በአገር ቤት እንዲካሄድ በአዘጋጅ ኮሚቴው በቀረበው መነሻ ሀሳብ ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ በትግራይ ክልል መዲና በሆነችው መቐለ የተካሄደው። “ትግራይ ለኢንቨስትመንት ምቹና ተወዳጅ ነች” በሚል መሪ ቃል የተከበረው ይþው ፌስቲቫል ከ

3 ሺ. ያላነሱ በቀጥታ ጥሪ የቀረበላቸው ዲያስፖራዎች የተሳተፉበት ነበር። የልማት ድግሱን ያሰናዳው የመቐለ ከተማ ህዝብም በተለመደው የእንግዳ አቀባበል ባህሉ ለረጅም አመታት ተለይተውት የቆዩ ውድ ልጆቹ ሲቀበል “ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ” እንዲሉ በታላቅ ደስታ ነበር የተቀበላቸው። የክልሉ ርዕሰ-መስተዳደር አቶ አባይ ወልዱ በፌስቲቫሉ የመክፈቻ ስነ-ስርዓት እንግዶቻቸውን ሲቀበሉ እንኳን የሀገራችሁን መሬት በሰላም ረገጣችሁ ነበር ያሏቸው። በመቀጠልም ፕሬዝዳንቱ ለክልላችን ልማትና ብልጽግና አብረን በመስራት ለልጆቻችን የተሻለች ትግራይ ብሎም ኢትዮጵያ ማስረከብ ጊዜ የማይሰጠው የቤት ስራችን ነው ሲሉ ተደምጠዋል።

ዲያስፖራዎቹ ደማቅ አቀባበል በተደረገላቸው ማግስትም በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ ኢንዱስትሪ ማዕከላትና የመሰረተ-ልማት ግንባታ እንቅስቃሴዎች ተዘዋውረው ጎብኝተዋል። ከጎበኟቸው ተቋማት መካከል መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግና ዩናይትድ ስቲልና ሜታል ኦንዱስትሪ ፋብሪካ ይገኙበታል። በመቀጠልም የአሸጎዳ ንፋስ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫና ተከዜ ሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጎብኝተዋል። በተመለከቱት ሁሉ መደነቃቸው በመግለጽ ሁሉም የኢትዮጵያ ዲያስፖራዎች በሀገራቸው ልማት መሳተፍ እንደሚጠበቅባቸው ዲያስፖራዎቹ ጠቁመዋል።

በሰማዕታት ሀውልት ቅጥር ግቢ ለተከታታይ ስድስት ቀናት ከፍት የተደረገው የልማት ኢግዚቢሽን ፌስቲቫሉን ካደመቁት ትዕይንቶች አንዱ ነበር። በኢግዚብሽኑ በግንባር ቀደምነት የተሳተፈው የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንም በጎብኚዎቹ ዘንድ አድናቆት ተችሮታል። በፌስቲቫሉ የተሳተፉ የክልሉ ተወላጅ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባዩዋቸው የኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ ምርቶችና የፕሮጀክት ክንውኖች በእጅጉ መደሰታቸውን በሰጡት አስተያየት ጠቅሰዋል። ለቀጣይም ከብኢኮ ጋር በቅርብ ትብብር መስራት እንደሚፈልጉ ተናግረዋል።

በተከታታይ ለስድስት ቀናት በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር የቆየው የትግራይ ዲያስፖራዎች ፌስቲቫል ሲጠናቀቅ የክልሉ ፕሬዝዳንትና ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችን ጨምሮ ከፍተኛ የፌደራል መንግስት ባለስልጣናት ዲፕሎማቶችና ቆንስላ ጀነራሎች ተገኝተዋል። ክልላቸውን በማልማት የወገናቸው ኑሮ እንዲቀየር በማለም ከመላው ዓለም እንደ ንብ ወደ ትውልድ ሀገራቸው የመሰባሰባቸው ሚስጢር ለዘለአለም ሲታወስ የሚኖር መልካም

ተግባር ነው ያሉት አቶ አባይ ወልዱ የክልሉ ብሎም የኢትዮÉያ ህዳሴ የዲያስፖራውን ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ሆኖ የተቀረጸ ነው ይላሉ። ለፌስቲቫሉ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ የተቀመጠለትን ግብ አሳክቶ መጠናቀቁን የጠቀሱት የክልሉ ፕሬዝዳንት ለፕሮግራሙ ስኬት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱ ልማት ማህበራት እና ግለሰቦች ምስጋና ችረዋቸዋል። የፌስቲቫሉ አዘጋጁ ኮሚቴ በበኩሉ ከተሰጡ ሽልማቶች ትልቁን ለታታሪውና የታሪክ ዕንቁ ለሆነው የትግራይ ህዝብ ሰጥተው፤ለህዝባዊ ወያነ ሐርነት ትግራይ ፣ ለትግሉ ሰማዕታትና በትግሉ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ሽልማት አበርክተዋል።

በእርግጥም ፌስቲቫሉ ከተጠበቀው በላይ ውጤታማ እንደነበር አብዛኞቹ አስተያየት ሰጪዎች ይስማማሉ። በፌስቲቫሉ በአካል የተገኙትም ሆነ ያልተገኙት ዲያስፖራዎች በየትኛውም የአለማችን ክፍል ሆነው በሀገራቸው ልማትና ብልጽግና ሂደት ለመሳተፍ የሚያግዳቸው አንዳች ሃይል እንደማይኖር አረጋግጠዋል። በዋናነት ከአምስት ክፍላተ-አህጉር ተሰብስበው ፌስቲቫላቸው በትውልድ ቀዬአቸው ያከበሩት እነዚህ ዲያስፖራዎች በክልሉ መንግስት ተጠንተው ለልማት ዝግጁ በሆኑ ሃምሳ ዓበይት ዘርፎች መዋለ-ንዋያቸውን ለማፍሰስ ፍላጎት አሳይተዋል። በቁጥር የማይናቁ ቀድመው የገቡ ዲያስፖራዎች ያፈሰሱት መዋዕለ ነዋይ ፈር እየያዘ እንደሚገኝም ልብ ማለት ያሻል።

በስተመጨረሻ የኢፌዲሪ መንግስት የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በሚፈቅደው አካሄድ መሠረት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በዲያስፖራዎቹ የፈጠረው ንቅናቄ በአብነት የሚጠቀስ ተግባር በመሆኑ በሌሎች የሀገራችን ክልሎችም ተጠናክሮ ቢቀጥል መልካም ነው ለማለት እንወዳለን።